# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

የግንቦት 7 ፡የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 22 ጥቅምት 6 2001 ዓ.ም


## መለስ ዜናዊ መንግስት የሶማሊያ ወረራ በሽንፈት እየተጠናቀቀ ነው።

የመለስ አገዛዝ ወታደሮች ከሶማሊያ በሽንፈት መውጣት እየጀመሩ ነው።የመለስ ወታደሮች ከሶማሊያ መውጣትን ተከትሎ በወታደሮቹ ጣልቃ መግባት ደም አፋሳሽ ሆኖ የሰነበተው የሶማሊያ እርስበርስ ግጭት ማብቂያ ሊሆን ይችላል ሲል በእንግሊዝ የሚታተመው ሰንዴይ ሄራልድ የተሰኘው እውቅ ጋዜጣ ዘገበ።እስቲቭ ብሉምፊልድ የተባለው የሰንዴይ ሄራልድ ጋዜጠኛ እሁድ ጥቅምት ሁለት 2001 ዓ.ም ከኬንያ ናይሮቢ እንደዘገበው የኢትዮጵያ ወታደሮች ከሶማሊያ ሲወጡ በቋፍ ላይ የነበረው የሶማሊያ የሽግግር መንግስት ህልውና ማክተሚያው ይሆናልም ብሏል። እንደ ስቲቭ ዘገባ እስልማዊ ታጣቂዎች በአሁኑ ጊዜ አብዛኛውን የሶማሊያ ደቡባዊና ማዕከላዊ ክፍል የተቆጣጠሩ ሲሆን ወደ ዋና ከተማዋ ሞቃዲሾ በመገስገስ ላይ እንደሆኑና በተለያዩ የከተማዋ ክፍሎች ጥቃት እያደረሱ እንደሆነም ገልጿል።

በአሜሪካን መንግስት ድጋፍ በህዳር ወር 1999 ዓ.ም የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረትን ከስልጣን ለማስለቀቅ ሶማሊያን የወረሩት የመለስ ወታደሮች ከሶማሊያ በመውጣት ላይም ይገኛሉ።

በጎረቤት ኬንያ የሚኖሩ የተለያዩ ሀገሮች ድፕሎማቶች እንደሚናገሩት የኢትዮጵያ ወታደሮች ከሶማሊያ እንደወጡ የሶማሊያው የሽግግር መንግስት መውደቂያው ስለሚሆን የሽግግሩ መንግስት ባለስልጣናትን ከሶማሊያ በስውር ለማስወጣት ዝግጅቱ እንደተጠናቀቀ ይህም በቅርቡ እንደሚከናወን ምንጮችን ጠቅሶ ጋዜጠኛው ዘግቧል።

የኢትዮጵያ ወታደሮች እና ታንኮች ከሞቃድሾ ወደብ ተጭነው ካለፈው ወር ጀምሮ በመርከብ መውጣት ጀምረዋል። አብዛኛው የሶማሊያ አካባቢ በእስላማዊ ታጣቂዎች ቁጥጥር ስለሚገኝ ወታደሮችንና መሳሪያዎቻቸውን በወታደራዊ ተሽከርካሪዎች ማጓጓዝ ሰላልተቻለ ኢትዮጵያ ወታደሮቿን ታንኮቿንና ከሞቃድሾ ወደብ በመርከብ በጅቡቲ አድርጋ ማሸጋገሯን በሶማሊያ ምድር የመለስ ወታደሮች መንቀሳቀስ እንዳልቻለ ማረጋገጫ ምልክት እንደሆነ ብዙ ተንታኞች ተናግረዋል።

ከተጀመረ በአንድ ሳምንት ግዜ ውስጥ ይጠናቀቃል የተባለው የሶማሊያ ወረራ፣አመታት መውሰዱና፣የብዙ ወታደር ሞትና ንብረት ኪሳራ ማስከተሉ ከመነሻው ዘመቻው የመለስ አገዛዝ ስህተት እንደሆነና፣በንጹሃን ሶማሊያውያንና የአገዛዙ ሰራዊት አባላት ላይ ለደረሰው የህይወትና የአካል ጉድለት መለስና አገዛዙ በቀጥታ ሙሉ የተጠያቂነት ሃላፊነት እንዳለባቸው አስተያየት ሰጪዎች ለግንቦት 7 ዜና ገልጸውልናል።

ግዜ

## የመያዶች ረቂቅ ህግ አለም አቀፍ ተቃወሞ ገጠመው።

“ረቂቅ ህጉ ሲቪክ ማህበራትን ያሽብራል፤ፓርላማው ህጉን የሚያጸድቅ ከሆነ ለጋሽ ሀገሮች የሚሰጡትን እርዳታ ሊያቆሙ እንደሚችሉ ለአገዛዙ ግልጽ ሊያደርጉለት ይገባል” ሲል የሰብዐዊ መብት ተሟጋች የሆነው ሂዩማን ራይትስ ዎች ጥቅምት 3 2001 ዓ.ም በመለስ አገዛዝ ተረቆ በያዝነው ወር ፓርላማው ያጸድቀዋል ተብሎ የሚቀቀውን ህግ አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ አስታውቋል።ረቂቅ ህጉ በኢትዮጵያ ለሰብዐዊ መብት መከበር መቆምን እንደወንጀል የሚቆጥር፣የእርዳታ ድርጅቶችንም የሚያፍንና የሚያሸብር ነው ሲልም አውግዞታል። አያይዞም ፓርላማው ህጉን ውድቅ እንዲያደርግም ጥሪውን አስተላልፏል። ሁማን ራይትስ ወች በመግለጫው እንዳስታወቀው ረቂቅ ህጉ መንግስት የእርዳታ ድርጅቶችንና ሲቪክ ማህበራትን እንዳሻው እንዲያስፈራራና እንዲያዳክም የሚያስችለው መሳሪያ ነው ብሏል።

የሂዮማን ራይትስ ወች የአፍሪካ ክፍል ዳይሬክተር ጆርጅ ጋግነን ይህ ረቂቅ ህግ ያስፈለገው በኢትዮጵያ ከግንቦቱ ምርጫ ተከትሎ ከተወሰደው የአፈና እርምጃ በኋላ ጥቂት የተረፉትን ገለልተኛ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሙሉ በሙሉ ለማጥፋትና ድምጻቸውን ለማዳፈን የታለመ እንደሆነ ገልጸው የመለስ አገዛዝ ይህን ህግ የሚያጸድቅ ከሆነ ለኢትዮጵያ እርዳታ የሚሰጡ መንግስታት የሚሰጡትን እርዳታ ሊያቆሙ እንደሚችሉ ለአገዛዙ ግልጽ ሊያደርጉለት ይገባል ሲሉ አስታውቀዋል። በረቂቅ ህጉ ለስራቸው ማስኬጃ ዘጠና በመቶ የሚሆነውን ገቢያቸውን ከውጭ የሚሰበስቡ አለምአቀፍ ድርጅቶች፣ ሀገር በቀል እና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ገንዘብ አዋጥተው የሚረዱአቸው የእርዳታ ድርጅቶች በሰብአዊ መብት ጥበቃ፣በሴቶች እኩልነት፣ በህጻናት መብት ጥበቃ፣ በአካለ ጉዳተኞች መብት ጥበቃ፣ ግጭቶችን በማስወገድ፣ የዳኝነት ስርዓቱን በማጠናከር እና ህግ በማስከበር ስራ፣ መልካም አስተዳደርን በማስፈን፣ በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ እና በመሳሰሉት ስራዎች እንዳይሳተፉ ይከለክላል።

### ግንቦት 7 ለፍትህ፣ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ

### በሳምንት ሶስት ቀናት ማለትም

**ማክሰኞ፣ሐሙስና ቅዳሜ ከምሽቱ 2:00 እስከ 2:30 ፤ በ17655 ኪሎ ኸርዝ በ16 ሜትር ባንድ ወይም በ21555 ኪሎ ኸርዝ በ13 ሜትር ባንድ ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚያሰራጨውን የሬዲዮ ፕሮግራም ይከታተሉ።**

በአሜሪካን ዜግነት ያለው ኢትዮጵያዊ ያውቃሉ?

ልጅ፣ ወንድም፣ እህት፣ የቅርብ ዘመድ፣ ጓደኛ ሊኖርዎት ይችላል፡፡ በፍጥነት ብእርዎን ወይም ስልክዎን ያንሱ ወይም ኮምፒተርዎን ያስነሱ፡፡ መልእክት ይላኩ፡፡ የዘንድሮ የአሜሪካን ምርጫ የእኛንም ሃገር ይመለከታል ይበሉ፡፡ በአሜሪካ የምትገኙ ወገኖቼ ውጡና ለምርጫ ተመዝገቡ፡፡ ኦባማን ምረጡ ይበሉ፡፡

ፕሬዚደንት ከሆንኩ ህዝባቸውን ከሚያሸብሩ አምባገነኖች ጋር አሜሪካ ወዳጅነት አይኖራትም ብለዋል ኦባማ፡፡ መለስ ዜናዊን አይነቶቹን አምባገነኖች ማለታቸው ነው፡፡

ኦባማን ማስመረጥ በመለስ ዜናዊ ላይ የሚገኝ የዲፕሎማሲ ድል ነው፡፡ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ እኛው በእኛው የምናደርገው ትግል ባይተካም፣አጋዥ ነው፡፡

# ርእሰ አንቀጽ

## የነጻ አውጭዎች ዘመን አክትሟል ሁሉም ለነጻነቱ ይነሳ!!

ትግል ረጅምና መራራ ነው ይባላል ። ውጣ ውረድ የሞላበት፤ አድካሚና እልህ አስጨራሽም ጭምር ። ከቤተሰብ ጉሮሮ ላይም ጊዜ ገንዘብና ህይወትን የሚነጥቅ ። ስለሆነም በዚህ በአድካሚና መራር ደረጃው ላይ ለመሳተፍ የሚፈቅዱ ጥቂቶች ናቸው ። እነዚህ ጥቂቶችም ትግሉ በሚጠይቀው መስዋእትነት የተነሳ ሳንጠግባቸው ያልፋሉ ። ጥቂቶች ለወሬ ነጋሪ ቢቀሩ እንኳ፤ የወደቁ ጓዶቻቸውን ህልምና ርእይ ከግቡ ሳያደርሱ በአዲስ ወጀብና ጎርፍ ይጠለፋሉ ። መስዋእትነት የጅሎች ድርጊት ያህል ይቆጠራል ። ለስልጣን መብቃት ራሱ እንደ ታላቅ እሴት ይወደሳል ። ባለስልጣንነትም እንደ ኒሻንና ሜዳሊያ በደረት የሚለጠፍ መጎናፀፊያ ፤ አብሮም ማስገበሪያና ብር መፈልፈያ መሳሪያ ይሆናል ። ይህንንም ንቅዘት ለመከላከል ደህንነት፤ አግአዚ፤ ተራራ ክፍለጦር፤ ወዘተ የግድ ይሆናል ። ብሎም በታጋይነት ተጀምሮ በንቅዘት የሚጠናቀቅ ለራስ የሚሰቀጥጥ ባዶ ድካም ይሆናል ። የደርጉ አባላት ለለውጥ የተዘጋጁ አስር አለቆችና ዝቅተኛ መኮንኖች ነበሩ ። የወያኔ መኳንንትም እንዲሁ ። ሁለቱም በለውጥ ጀምረው በንቅዘት የተጠናቀቁ ለመሆን ከመብቃታቸው ብዙ እንማራለን ። አንዱ ትልቁ ትምህርት የስልጣን ጥመኞችን፣ አድር ባዮችን፤ በትግሉ ወቅት የዴሞክራሲ መብቶች እንዲታቀቡ ጥብቅና የሚቆሙትን፤ ከመስዋእትነት በመሸሽ በህይወት ለመቆየት የሚያሴሩትን፤ የመለስና መንግስቱ አይነት ደካሞችን ከትግሉ ማጥራትም ተገቢ መሆኑን ነው ።

ከሁሉም በላይ ግን ታላቁ ችግር ፤ ትግሉ የጥቂት ጀግኖች ሃላፊነት ተደርጎ መታየቱ ነው ። በትግሉ ወቅት ለመታገል ዳተኛ የነበሩ በድል አጥቢያ አርበኝነት በድሉ ወቅት ሲቀላቀሉ፤ ይዘውት የሚመጡት አድርባይነትና ለባለስልጣን ማጎብደድ ከማንኛውም ነገር የበለጠ ትግሉን የሚጎዳ መሆኑ ተደጋግሞ በራሳችንም ሆነ በሌሎች ሃገሮች ትግሎች የታየ ጉዳይ ነው ። ሃገራችን የጀግኖች ሃገር ናት የሚባለውም ያለምክንያት አይመስለንም ። በየፈታኙ የሃገራችን ምእራፍ የእመ-ኢትዮጵያ ፍቅራቸው እንቅልፍ የሚነሳቸው ጀግኖች፣ እንደ ጧፍ እየቀለጡ ነፃነቷን ጠብቀው ያቆዩዋት ሃገር በመሆንዋ ነው ። ከግራዚያኒ እስከ መለስ በየወቅቱ አገዛዝን እየተቃወሙ መስዋእት የሆኑ ጀግኖች ፤ ከህዝቡ ተነጥለው ብቻቸውን ቆመው የሚቀጠቀጡበትን የታሪካችንን ምዕራፍ እልባት ልናደርግበት ይገባል ። ድሉ ብቻ ሳይሆን ትግሉም የመላ ህዝቡ መሆን ይኖርበታል ። የጥቂቶች ጀግንነት አክትሞ ፤ የብዙሃን ታሪክ ሰሪነት የሚተካበትን መላ መፈለግ ይኖርብናል ። ማንም ማንንም ነፃ የማውጣት ተልእኮ ሊኖረው እንደማይችል ልንረዳ ይገባል ። በአንድ ገፁ የገገርዎቻችን ምንነትና ማንነት፤ የደካማነታችን ማንፀባረቂያ መስተዋትም ጭምር መሆኑን ልንረዳ ይገባል ። መለስን የመሰለ ጭንጋፍ ለኢትዮጵያችን ክብር የማይመጥን ስድብ ሆኖ ሊሰማን ይገባል ። በግላችንም መብሰልሰልና መበሳጨት አቁመን፤ በራችንን ዘግተን ማልቀስ ትተን፤ ልጆቻችን በረሃብና ጠኔ በቁማቸው ሲጠወልጉ እያየን ወደውስጣችን ማልቀሱን ትተን፤ ፈጣሪያችን የሰጠንን ሰብአዊ ክብር ላለማስነካት መታገል ይኖርብናል ። አንጋጠን የምንጠብቃቸው ጥቂት ጀግኖች ከእንግዲህ ሊኖሩን አይችሉም ። ጀግንነት የእያንዳንዳችን የክብር መጎናፀፊያ እንጂ ፤ ለጥቂት ቆራጦች የተሰጠ ልዩ ፀጋ አይደለም ። ያልዘራነውን ማጨድ እንዳይቻለን ሁሉ ያልታገልንበትንም እንዳናገኝ የማይጠረጠር ነው ።

**የመያዶች ረቂቅ ህግ** ከገጽ 1 የዞረ

በረቂቅ ህጉ የእርዳታ ድርጅቶችን እና ሲቪክ ማህበራትን የሚቆጣጠር አካል እንዲቋቋም የተደነገገ ሲሆን ተቆጣጣሪው አካል በማህበራቱ ላይ ምንም አይነት እርምጃ ቢወስድ ይግባኝ ማለት እንዳይችሉ የሚያደርግና የተቆጣጣሪው ባለስልጣናት በማናቸውም ጊዜ ያለ በቂ ምክንያት ማህበራቱን ላለመመዝገብ እንዲችሉ የሚያደርግ፣ የድርጅቶቹን መሪዎች በፈለጉ ጊዜ እንዲያባርሩ የሚፈቅድላቸው እና ድርጅቶቹ ስራቸውን በአግባቡ እንዳይወጡ የተለያዩ እንቅፋቶችን የሚፈጥር ነው ሲል ሁማን ራይትስ ዎች ክፉኛ ነቅፎታል፡፤

ምንም እንኳን የአገዛዙ አፈቀላጤዎች ህጉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተጠያቂነት ያለውን አሰራር እንዲከተሉ የሚያደርግ ነው ቢሉም ሁማን ራይትስ ዎች ግን እንዲህ አይነት አፋኝ ህግ ሳያረቁ የሲቪክ ማህበራት በሚሰሩት ስራ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚቻልና በአፍሪካ ያሉት ሀገሮች ለምሳሌ ማላዊ፣ ታንዛኒያ እና ደቡብ አፍሪካ እንደ ኢትዮጵያ ያለ አፋኝ ህግ ማርቀቅ ሳያስፈልጋቸው በሀገራቸው ያሉ የሲቪክ ማህበራት በስራቸው ተጠያቂነት ያለውን አሰራር መከተል እንዲችሉ ማድረጋቸውን ገልጾ የአገዛዙ ሃላፊዎች የሚሰጡትን ምክንያት ውድቅ አድርጓል።

እንደ ሁማን ራይትስ ዎች አሁን የተረቀቀው ህግ የመለስን የራሱን ህገ መንግስት፣ በተለያዩ ጊዜያት ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ውሎችንና የአለምአቀፍ የሲቪክ እና የፖለቲካ መብት ድንጋጌዎችን የሚጻረር እንደሆነ ገልጿል። እንደ አፍሪካ ህብረት መቀመጫነቷ ለሌሎች የአፍርካ ሀገሮች በመልካም አስተዳደር አርአያ መሆን ይገባት ነበረ እንጂ ሲቪክ ማህበራተን በማፈን መጥፎ ምሳሌ ልትሆን አይገባትም ነበር ብለዋል የሁማን ራይትስ ወች የአፍሪካ ዳይሬክተር።

የመለስ አገዛዝ በጸረ ሽብርተኝነት ሰበብ የአሜሪካ ሽሪክ በመሆኑ ከተለያዩ ለጋሽ ሀገሮች በየአመቱ አንድ ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እርዳታ እንደሚያገኝ ሪፖርቱ አስታውሶ እንዲያውም ለጋሽ ሀገሮች በተለይም አሜሪካ፣ እንግሊዝ እና ፈረንሳይ የመለስ አገዛዝ እየፈጸመ ያለውን የሰብአዊ መብት ረገጣ በአደባባይ ማውገዝ ሲገባቸው በስውር ከመለስ አገዛዝ ጋር ውይይት በማድረግ መሻሻሎች ማምጣት እንችላለን በሚል ስሌት ግንኙነታቸውን ጠብቀው ቢቀጥሉም እስካሁን ያደረጉት ውስጥ ለውስጥ ድርድር ምንም ፋይዳ ያላመጣ እንደሆነ ገልጿል።

እንደ ሁማን ራይትስ ወች እንዲያውም ባለፉት ሁለት አመታት የመከላከያ ሰራዊቱና የደህንነት ሀይሎች በሀገር ውስጥና በጎረቤት ሀገር ሶማሊያ የጦር ወንጀልና በስብዕና ላይ የሚደረግን ወንጀል ቢፈጽሙም እስከአሁን ተጠያቂ አልሆኑም። ስለዚህ እስካሁን ለጋሽ ሀገሮች በስውር እናደርጋለን ያሉት ድርድር ምንም ፋይዳ ያላመጣ እንደሆነ ተገንዝበው በንጹሓን ዜጎች ላይ የሚፈጸመው ሰብአዊ መብት ረገጣ በዚህ አይነት የሚቀጥል ከሆነ የሚሰጡትን የገንዘብ ድጎማ ሊያቋርጡ እንደሚችሉ ለመለስ ዜናዊ መንግስት ግልጽ ሊያደርጉለት ይገባል ሲል ሪፖርቱን ደምድሟል።

ግንቦት 7 ድምጽ በግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

# የፖለቲካ ትንትና

በዚህ አምድ ስር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣጥፎች ይቀርባሉ

## ከክህደት ወደ እምነት ጽናት ፍቅሩ

ካለፈው ሰሞን የኢህአዴግ ጉባኤ የምንማረው ነገር አለ?ብዮ እራሴን ጠየቅኩ፣መልሱንም እራሴው መለስኩ እንዲህ በማለት አዎ! አለ እንጅ። ግን መግደልና ማሰርን አይጨምርም። እንዲያውም አንዳንድ ፖሊሲዎች ሲነደፉ ብዙ ጊዜ መሰረት የሚያደርጉት የተቃራኒ ወገንን ሀሳብና ፍላጎት ነው። ለምሳሌ የውጭ ፖሊሲዎች ሲነደፉ፣ የሌሎችን አገሮች ፖሊሲዎች ማወቅ የግድ ይላል። (የኢህአዴግን የዘፈቀደ የውጭ ፖሊሲ ማለቴ አይደለም። ኢህአዴግ ሲሻው ዛሬውኑ ፖሊሲ ነድፎ ያድራል።) የጦር እቅድም ሲነደፍ የጠላትን አሰላለፍና አቋም መነሻ በማድረግ ነው። በተመሳሳይም ግንቦት 7 ፖሊሲውን ሲነድፍ የኢህአዴግን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ እንዳስገባ እገምታለሁ። የተቃራኒን ወገን የሀይል አሰላለፍ ለማወቅ ካልተቻለ፣ የራስን የሀይል አሰላለፍ ለመወሰን አይቻልም። ስለላ የመጣውና የሚያስፈልገውስ ለዚህ አይደል። በዚህ እምነትም ከሰሞኑ የኢህአዴግ ጉባኤ አንዳንድ ነገሮችን በመንቀስ ፖሊሲን ማስተካከል እንደሚቻል ለማሳየት እሞክራለሁ ።ከአዋሳው ጉባኤ ሁለት ነገሮች ነጥረው ወጥተዋል። ሁለቱም ነገሮች የኢህአዴግን ፍጻሜ መቃረብ የሚያሳዩ ናቸው።አንዱ የአባላት ድርቅ ሲሆን ሌላው ደግሞ የእምነት መጥፋት ነው።

ሀ) የአባላት ድርቅ

ኢህአዴግ የአባላት እጥረት እንዳለበት በይፋ ተናግሯል። አባባሉ፣ በቅርቡ አራት ሚሊዮን አባላት አሉኝ ብሎ ከተናገረው ጋር የሚጋጭ ይመስላል። ኢህአዴግ በቁጥር 4 ሚሊዮን አባላት አሉት፣ በጥራት ግን ምንም ሰው የለውም። ይህን ደግሞ እኔ ሳልሆን እነመለስና በረከት የተናገሩት ነው፡፡ አብዛኞቹ የኢህአዴግ አባላት አባል የሚሆኑት በፕሮግራሙ አምነው ሳይሆን ለስራ ፍለጋ ነው። እነመለስ እንደነገሩን ከሆነ ብዙዎቹ ስራ ከያዙ በሁዋላ ግንባሩን “ አዲዮ” ይሉታል። ስለዚህ የእነ መለስን ዘረኛ ፖሊሲዎች የሚያራምዱ ሰዎች ቁጥር እየተመናመነ ነው። ይህ ማለት አብየታዊ ዲሞክራሲን የሚያራምዱት የአሁኖቹ መሪዎች በሞት ወይም በሌላ መንገድ ቁጥራቸው ሲቀንስ፣ ግንባሩ ተንገራግጮ ይወድቃል ማለት ነው። በሩሲያ የሆነው ይህ ነው። የመጀመሪያዎቹ የኮሚኒስት አቀንቃኞች ሲያልቁ፣ ተተኪዎቻቸው ሌላ አስተሳሰብ ይዘው ቀጠሉ። እነ ጎርባቾቭ የመጀመሪው ትውልድ አባላት አልነበሩም። ኢህአዴግም የመጀመሪያውን ትውልድ አባላት በሞት፣ በእርጅናና በጠብ እያጣ ነው። ከትንሽ ጊዜ በሁዋላ አብዮታዊ ዲሞክራሲን በቆሻሻ መጣያ ውስጥ እንኳን ፈልገን አናገኘውም።እንደ ማርኪስዝም አስተሳሰብ አለማቀፋዊ ቢሆን ኖሮ፣ በአንዳንድ የመጽሀፍ መደርደሪያዎች እናገኘው ነበር። ይህ ግን ወንዝ የማያሻግር፣ ዳቦ የማይጋግር፣ መርዘኛ አስተሳሰብ ነውና እጣ ፋንታው ከማርኪስዝም ፍልስፍናም በብዙ እጅ የከፋ ነው።ሲኦል ከመውረድና ከመቃጠል ውጭ ሌላ እድል የለውም። ማርክሲዝምስ በትንሳኤ ቀን ሊነሳ ይችላል። እየሱስ ከሀይማኖቱ በስተቀር፣ አሪፍ ኮሞኒስት አልነበር። በአጭሩ አብዮታዊ ዲሞክራሲ በጥቂት አምባገነኖች አእምሮ ውስጥ ያለ በመሆኑ እነርሱ ሲሞቱ፣ ወይም ከዚያ በፊት ቀብሩን እንሰማለን።

የኢትዮጵያ ወጣቶች አብዮታዊ ዲሞክራሲ እያሉ በብሄርና በአረጀ ፍልስፍና ታጥረው እንዲኖሩ የአለም ሁኔታ አይፈቅድላቸውም። እድሜ ለቴክኖሎጂ፣ አለም እየተቀራረበች ነው። ወጣቶቹ ስለሌላው አለም አኗኗር መረጃ በቀላሉ የሚያገኙበት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል ወጣቶቹ እራሳቸውን ከአዲሱ አስተሳሰብና ከአለም ነባራዊ ሁኔታ ጋር ለማወዳደር አይቸግራቸውም። ምናልባትም ከትግሬነት ወይም ከአማራነት በላይ በቅድሚያ ሰው መሆናቸውን፡ ከሌላው አለም ሰው ጋር ለመገናኘት ትግሬ ወይም አማራ መሆናቸው እንደማያግዳቸውና ራሳቸውን በብሄር አጥረው ከጭዋታ ውጭ ከሚኖሩ፣ አለማቀፍ ሰው መሆን እንደሚሻላቸው ሊያምኑ ይችላሉ። አሁን የመለስ ልጅ እንደናቷና እንደአባቷ የዘረኝነት አስተሳሰብ አይኖራትም። አብዮታዊ ዲሞክራሲ ምን እንደሆን የምታውቀውም አይመስለኝም።እድሜ ለትምህርትና ለምትማርበት ትምህርት ቤት! በውጭ አገር በመማሯ ከብዙ ባህሎችና አስተሳሰቦች ጋር እንድትገናኝ እድል ገጥሚታል። ከጫካ አስተሳሰብ ወጥታ፣ የሳይበር አስተሳሰብ ይዛለች።እንዳባቷና እንደናቷ እራሷን ልዩ የትግራይ ልጅ አድርጋም አትቆጥርም። አባቷ በጫካ ውስጥ ከቀረጸው አስተሳሰብ ፈጽሞ የተለየ አስተሳሰብ እንደያዘች የምናውቀው ጓደኞቿን በማየት ብቻ ሳይሆን በእንግሊዝ ትምህርት ቤት መማሯን ግምት ውስጥ በማስገባት ጭምር ነው( በእንግሊዝ ትምህርት ቤት የተማሩ አምባገነን መሪዎችን አልረሳሁም)። ቢያንስ ወጣት ተማሪዎች ተቃውሞ ሲያሰሙ እንደማይገደሉ ከእንግሊዞች ተምራለች። አብዮታዊ ዲሞክራሲ ደግሞ አመለካከትን በጠመንጃ ለማፈን የሚሞክር አስተሳሰብ ነው።ስለዚህ የመለስ ልጅ አብዮታዊ ዲሞክራሲን ታጥቃ ትኖራለች ብሎ ማሰብ ከባድ ይሆናል። ለሌላው ወጣትም እንዲሁ ነው።ለኢህአዴግ ብቻም ሳይሆን ለሁሉም ይሰራል። ኢህአዴግ አብዮታዊ ዲሞክራሲን የሚሸከሙ ወጣቶችን ማግኘት አልቻልኩም የሚለው በቴክኖሎጂ ምክንያት ብቻ ሳይሆን አስተሳሰቡ ደሀ በመሆኑ ጭምር ነው። አብዮታዊ ዲሞክራሲን ስናስብ አብሮ የሚታየን ዘረኝነት፣ ድንቁርና፣ ጉራና ጥላቻ ብቻ ነው። ጤነኛ ሰው ይህንን እንዴት ሊሸከም ይችላል?

ከስብሰባው ያገኘነው ትልቁ ድል ኢህአዴግ አባላትን ለመመልመል የሚጠቀምበትን ዘዴ ይፋ ማድረጉ ነው። ይህን መንገድም ለአመታት ሲክደው ነበር።ወጣቶች የኢህአዴግ አባል ካልሆኑ ስራ ማግኘት እንደማይችሉ ባለስልጣኖቹ ተናግረዋል። ለማረጋገጫ የበረከትን ንግግር ከልሳኖቻቸው ከእነ ሪፖርተር ማግኘት ትችላላችሁ። ድርጊቱ ትልቅ የሰብአዊ መብት ሲጣስ መቆየቱን የሚያመለክት ነው። አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች፣ ዜጎች በነጻነት ስራ የማግኘትና ሰርተው የመኖር መብት አላቸው ይላል። ይህ ማለት የማንም የፖለቲካ ድርጅት አባል ሳይሆኑ በዜግነታቸው ብቻ ስራ የማግኘት መብት አላቸው ማለት ነው። ይህ መብት ዜጋ መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን፣ ከሌሎች ዜጎች የሚለያቸው መሆኑንም የሚያሳይ ነው። በአገራቸው እንደሚኖር የውጭ አገር ዜጋ የስራ ፈቃድ አውጡ አይባሉም። እንግዲህ ወጣቶች ስራ ለመቀጠር የኢህአዴግ አባል መሆን ካለባቸው፣ የሚያጡት መብታቸውን ብቻ ሳይሆን ዜግነታቸውን ጭምር ነው ማለት ነው። ኢህአዴግ ወጣቶችን ዜግነት አልባ እያደረጋቸው ነው ማለት ነው። ይህም ትልቅ ወንጀል ነው። ጸሀፊው ተከሶበት ከነበረው ያገር ክዳት ወንጀልም በላይ ነው።

ድርጊቱ ከሰብአዊ ጥሰት በተጨማሪ ሌሎች ብዙ ነገሮችንም ያሳየናል። እነዚህ ሰዎች በፓርቲ አባልነታቸው ስራ በመያዛቸው በራስ መተማመን አይኖራቸውም። አንድ ቀን ብንባረር ወይም የሚመጣው መንግስት ያለብቃት ማረጋገጫ ነው የተቀጠራችሁት ብሎ ቢያባርረን እያሉ ስለሚሰጉ፣ ያገኙትን አጋጣሚ ተጠቅመው ገንዘብ ለመሰብሰብና ለመጥፋት ያልማሉ። ሙስና በየጊዜው እየጨመረ የመጣውም በከፊል በዚህ ምክንያት ነው። ሰራተኞቹን የሚያሰጋቸው ለወደፊቱ የሚመጣው ችግር ብቻ ሳይሆን ፣ በብቃት ማነስ የተነሳ ህዝቡን ማገልገል አለመቻላቸው ጭምር ነው። የአዲስ አበባ መስተዳድር ወቅታዊ ሁኔታ ጥሩ ማሳያ ነው። ሰራተኞቹ በብቃት ተመዝነው ባለመግባታቸው፣ ጥሩ ሰራተኛ ሊሆኑ አይችሉም። ስራ ከማበላሸት ጀምሮ ያሉትን መጥፎ ድርጊቶች ሁሉ ይፈጽማሉ። የኢህአዴግ ፖሊሲ “ውሀ ቢወቅጡት እንቦጭ” የሆነውም ባንድ ምልኩ ለዚህ ነው። ( ይቀጥላል)

# ሃይለ ሀሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

## ለህዝብ፤ካልሆነ፡ለማን፡ለአገር፡ካልሆነ፡ለምን?

በአፍሬም፡ማዴቦ

ብዙዎቻችን፡ኢትዮጵያ፡ምን፡ያስፈልጋታል፡በሚል፡ሰፋ፡ያለ፡ጥያቄ፡እራሳችንን፡ስናስጨንቅ፡እንታያለን።ኢትዮጵያ፡ችግርዋ፡ብዙ፡የሚያስፈልጋትም፡ብዙ፡ነዉና፡የእያንዳንዳችን፡ተቀዳሚ፡ተግባር፡ኢትዮጵያ፡ምን፡ያስፈልጋታል፡የሚለዉን፡ሳይሆን፡ኢትዮጵያ፡ከእኔ፡ምን፡ትፈልጋለች፡የሚለዉን፡ጥያቄ፡መመለስ፡ነዉ፡፡ኢትዮጵያዊ፡ሆኖ፡ተፈጥሮ፡ይህንን፡ጥያቄ፡የማይመልስ፡ዜጋ፡አለ፡ብዬ፡አላምንም።ችግሩ፤አንዳንዶቻችን፡ለኢትዮጵያ፡ማድረግ፡የምንፈልገዉ፡ኢትዮጵያ፡ከእኛ፡የምትፈልገዉን፡ሳይሆን፡እኛ፡ለኢትዮጵያ፡የምንፈልገዉን፡ነዉ።ለምሳሌ፡በግንቦት፡1983አ.አበባን፡የተቆጣጠሩት፡ወያኔዎች፡በዉል፡ያልተገነዘብዋትንና፡የማያዉቅዋትን፡ኢትዮጵያን፡ለማወቅና፡ለመገንዘብ፡ከመሞከር፡ይልቅ፡ኢትዮጵያ፡እነሱን፡እንድታዉቃቸዉና፡እነድትገነዘባቸዉ፡በሀይል፡ጭምር፡በመሞከራቸዉ፡እነሱ፡ኢትዮጵያን፡ኢትዮጵያም፡እነሱን፡ሳታዉቃቸዉ፡ድፍን፡170መት፡አለፈ።በመጠሪያ፡ስሙ፡ፊትለፊት፡“ህዝባዊ”የሚል፡ቅፅል፡የቀፀለና፡ህዝባዊ፡ስርአት፡እገነባለሁ፡የሚል፡መንግስት፡ከምንም፡ከማንም፡በፊት፡የሚያስቀድመዉ፡ህዝብን፡ነዉ።ህዝብን፡የሚያስቀድም፡መንግስት፡ደግሞ፡የህዝብ፡አለኝታ፡የሆነዉን፡የአገር፡ዳር፡ድንበር፡ይጠብቃል፡እንጂ፡ሠላማዊ፡ዜጎችን፡በየአደባባዩ፡አይገድልም፡ወይም፡ስግብግብ፡ፍላጎቱን፡ለሚያሟላለት፡የዉጭ፡መንግስት፡ መሬት፡እየቆረሰ፡አይሰጥም።

ህዝብ፡ይቅር፡ባይ፡ነዉና፡የበደሉትን፡ይቀር፡ሊላቸዉ፡በደላቸዉንም፡ሊረሳ፡ይችላል።ነገር፡ግን፡ተከታታይ፡ትዉልድ፡በደሙ፡ያጠረዉን፡መሬት፡በማን፡አለብኝነት፡ለሌላ፡የሚሰጥንና፡ህዝብን፡በአካል፡ብቻ፡ሳይሆን፡ስሜቱንም፡ጭምር፡የሚገድልን፡የለየለት፡የህዝብ፡ጠላት፡ህዝብ፡እስከ፡መጨረሻዉ፡ይፋረደዋል፡እንጂ፡በይቅር፡ብዬሀለሁ፡ብቻ፡አያልፈዉም።ወያኔን፡የምንለካዉ፡እሰራለሁና፡አደረጋለሁ፡እያለ፡በየጠዋቱ፡በሚሰጠን፡ባዶ፡የተስፋ፡ቃል፡ሳይሆን፡እስከዛሬ፡በሰራቸዉ፡ስራዎቹ፡ነዉ።ዛሬ፡የአገራችን፡ኤኮኖሚ፡አደገ፡እየተባለ፡ይፎከራል፤የኢትዮጵያ፡ህዝብ፡ግን፡እምነቱ፡ረድቶት፡መንፈሱን፡በልጆቹ፡ተስፋ፡እየመገበዉ፡ነዉ፡እንጂ፡የሚላስ፡የሚቀመስ፡ካጣ፡ቆይቶአል።ለወትሮዉ፡ድርቅና፡ረሀብ፡ጅምሩ፡ላይ፡ቢደበቅም፡የማታ፡የማታ፡እርዳታ፡ይጠየቅ፡ነበር።የዘንድሮዉ፡ለጉድ፡ነዉ!

አረንገዴዉ፡የአገራችን፡ክፍል፡የሚበላ፡አጥቶ፡ረሀብ፡በአገሪቱ፡የለም፡እየተባለ፡ነዉ።ደርግን፡አሸንፈዉ፡አ.አበባ፡ሲገቡ፡ሙሉ፡ልብስ፡የሚገዛ፡የባንክ፡ሂሳብ፡ያልነበራቸዉ፡ወያኔዎች፡“ድህነት፡አያሳፍርም”ይልቁንም፡ሊያሰራን፡ይገባል፡እያሉ፡ይሸነግሉናል።አባባሉ፡መልካም፡ነበር፡ወሬ፡ብቻ፡ ሆነ፡እነጂ

የብልሹዉ፡የኢትዮጵያ፡መስተዳድር፡ቁንጮ፡የሆኑት፡ስግብግብ፡የወያኔ፡መሪዎችና፡ጀሌዎቻቸዉ፡ሊያሳፍራቸዉ፡የሚገባዉ፡የኢትዮጵያ፡ድህነት፡ሳይሆን፡በዚያች፡ደሃ፡አገር፡ዉስጥ፡የእነሱ፡በአጭር፡ግዜ፡ዉስጥ፡መጠን፡የለሽ፡ሀብታም፡መሆን፡ነዉ።ህዝብን፡የሚያገናኝ፡ድልድይ፡ሳይሆን፡የሚለያይ፡ግድድዳ፡መገንባት፡የሚቀናዉ፡ወያኔ፡እኛ፡ኢትዮጵያዉያን፡“ኢትዮጵያ“የሚለዉን፡ትልቅ፡ሀሳብ፡ትተን፡በጎጠኝነትና፡በጎሳ፡ፖለቲካ፡ላይ፡እንድናተኩር፡እያደረገ፡ነዉ።የሰዉ፡ልጅ፡በሰዉነቱ፡አንዱ፡ከሌላዉ፡እንደማይለያይ፡በዉል፡የተገነዘበዉ፡የኢትዮጵያ፡ህዝብ፡ግን፡ጎጠኞች፡በገነቡት፡አጥርና፡ግድግዳ፡አልለያይም፡ብሎ፡በአንድነቱ፡ፀንቶ፡ቆሞአል።ከህዝብ፡ጋር፡አብሮ፡መኖርንና፡የማህረሰብን፡ሁለንተናዊ፡ህብረት፡በምናቡም፡ሆነ፡በገሀዱ፡ዓለም፡ያልተለማመደዉ፡ወያኔ፡የራሱን፡ህይወት፡በህዝብ፡አይን፡የህዝብን፡ህይወት፡ደግሞ፡በራሱ፡አይን፡መመልከት፡አይችልም።ስለሆነም፡ወያኔ፡ከጠባብ፡ብሔረተኝነትና፡ከማይረካ፡የሥልጣን፡ጥማቱ፡ተላቅቆ፡የኢትዮጵያን፡ህዝብ፡የነፃነትና፡የፍትህ፡ፍላጎት፡ያሟላል፡ማለት፡ዘበት፡ነዉ።

የቀድሞዎቹ፡የኢትዮጵያ፡መንግስታት፡የተከተሉት፡የተዛባ፡የኤኮኖሚና፡የፖለትካ፡ፖሊሲ፡በአንዳንድ፡የአገሪቱ፡ብሔረሰቦች፡መካከል፡አለመረጋጋት፡መፍጠሩ፡የሚታወስ፡ነወ።ሆኖም፡ዛሬ፡በአገሪቱ፡ብሔረሰቦች፡መካከል፡በተለይም፡ደቡብ፡ኢትዮጵያ፡ዉስጥ፡በጉጂና፡በቡርጂ፡ብሔረሰቦች፡መካከል፡የታየዉ፡የእርስ፡በእርስ፡መተላለቅ፡የወያኔ፡እብሪት፡አርግዞ፡የኢህአዴግ፡ክፋት፡የወለደዉ፡ሰዉ፡ሰራሽ፡ችግር፡ነዉ።የዲሞክራሲ፡ሠልፈኞችን፡በመተረየስ፡እየጨፈጨፉ፡ፀጥታ፡ለማስከበር፡ነዉ፡እያሉ፡የሚወሰልቱት፡የወያኔ፡መሪዎች፡ሁለት፡ወር፡በማይሞላ፡ግዜ፡ዉስጥ፡የጉጂና፡የቡርጂ፡ብሔረሰቦች፡ሁለቴ፡ጦርተማዝዘዉ፡ሲገዳደሉ፡በዝምታ፡መመልከታቸዉ፡ወያኔ፡ሆን፡ብሎ፡ችግር፡የሚፈጥርና፡የሚያባብስ፡እንጂ፡ችግር፡የማስወገድ፡ፍላጎት፡የሌለዉ፡መንግስት፡መሆኑን፡በተግባር፡አሳይቶአል።

የኢትዮጵያ፡ህዝብ፡ሆይ!

ወያኔ፡ኑሮህን፡የምድር፡ላይ፡ሲኦል፡አድርጎታል፡ሆኖም፡በህይወት፡መኖርህን፡ላፍታም፡ቢሆን፡ልትጠላዉ፡አይገባም።ህይወት፡ፈጣሪ፡የሰጠህ፡ፀጋ፡ነዉና።ሞትንም፡ቢሆን፡ልትፈራ፡አይገባም፡መከፈሉ፡የማይቀር፡ዕዳ፡ነዉና።ልታስብበትና፡ልትጠነቀቅለት፡የሚገባህ፡ከህይወትህ፡መጀመሪያ፡እስከ፡ህይወትህ፡መጨረሻ፡ያለዉን፡የሽግግር፤ወቅት፡ነዉ።ይህ፡ወቅት፡መንግሰት፡አንተን፡አንተ፡ደግሞ፡አገርህንና፡ቤተሰብህን፡የምታገለግልበት፡ወርቃማ፡ግዜ፡እንጂ፡አፍህ፡እንዳይበላም፡እንዳይናገርም፡ተለጉሞ፡በገዛ፡አገርህ፡ተረግጠህና፡ተንቀህ፡የምትኖርበት፡ወቅት፡አይደለም።ኢትዮጵያ፡ዉስጥ፡ህዝብን፡የማያስቀድም፡መንግስትና፡የአገርን፡አንድነት፡የማያስጠብቅ፡መሪ፡እንኳን፡170መት፡አንድ፡ቀንም፡ሊኖር፡አይገባም።

እኛ፡የህዝብ፡ወገኖች፡ስላለፈዉ፡አናለቅስም፡የወደፊቱንም፡አንፈራም።ህዝባዊ፡ትግላችንን፡በአሸናፊነት፡የምንወጣዉ፡ዉስጣችን፡ያለዉን፡ፍርሀት፡ስናምቀዉ፡ሳይሆን፡ፊትለፊት፡ስንጋፈጠዉ፡ነዉ።ከፍርሀታችን፡ሁሉ፡እጅግ፡የከፋዉ፡ፍርሀት፡ትክክለኛዉን፡መንገድ፡እያወቅን፡ፈርተን፡ሳንራመደዉ፡ስንቀር፡ነዉ።እኛዉ፡እራሳችን፡ቦታ፡ሰጥተነዉ፡ነዉ፡እንጂ፡ወያኔማ፡የራሱን፡ጥላ፡የሚፈራ፡<u>ቦቅበቃ</u>፡ፍጥርት፡ነዉ።ሚስጢሩ፡ቢገባን፡የወያኔ፡ድፍረት፡እኛ፡በፈራነዉ፡ልክ፡የኛ፡ፍርሀት፡ደግሞ፡የራሳችን፡ስነልቦና፡በፈቀደዉ፡ልክ፡ነዉ።

የለየላቸዉ፡ጠላቶቻችንና፡አንዳንድ፡ግራ፡የገባቸዉ፡ወዳጆቻችን፡የሚጮሁብን፡አሉታዊ፡ጩኸት፡ቀርቶ፡አንዳንዴ፡የራሳችን፡ደመነብስ፡በለሆሳስ፡ትንፍሽ፡የሚልብን፡የድካም፡ስሜትም፡ቢሆን፡ከተነሳንለት፡ትክክለኛ፡አላማ፡ፍንክች፡አያደርገንምበድል፡ያሸበረቀ፡ታሪክ፡ላለዉ፡ህዝብ፡በጥቂቶች፡ተሸንፎ፡መኖር፡ዉርደት፡ነዉ፡ከዚህ፡ዉርደት፡ለመላቀቅ፡ምንም፡አለማድረግ፡ደግሞ፡ከዉርደትም፡በላይ፡የቁም፡ሞት፡ነዉ።የህይወት፡አዘቅት፡ዉስጥ፡የተጣለ፡ህዝብ፡መዉደቅ፡አይፈራም፡፡ ዬት፡እንዳይደርስ?

የኢትዮጵያ፡ህዝብ፡ሆይ!

የልብህን፡ትርታ፡የዳመጡ፡ልጆችህ፡ያዋጣናል፡ላንተም፡ይበጃል፡ያሉትን፡የትግል፡ስልት፡መርጠዉ፡የአንተ፡ነፃነት፡ሳይረጋገጥ፡የማይቆም፡የትግል፡ጉዞ፡ጀምረዋል።የወያኔ፡የፈሪ፡ዱላ፡ለግዜዉ፡ቢጠነክርም፤የአግአዚዉ፡ጀሌና፡የመሳሪያ፡ብዛቱ፡የሚያስፈራ፡ቢመስልም፡እኛን፡ሊያሳስበን፡የሚገባዉ፡ወያኔ፡ምን፡ያደርገናል፡የሚለዉ፡ጥያቄ፡ሳይሆን፡እኛ፡ነፃነታችንን፡ለማስመለስ፡ምን፡ማድረግ፡አለብን፡የሚለዉ፡ጥየቄ፡ነዉ።ወያኔማ፡አሁን፡ከሚያደርገዉ፡ሌላ፡ምን፡ሊያደርግብን፡ይችላል?የኢትዮጵያ፡ህዝብ፡ሆይ!

ህልማችን፡አንተ፡በልፅገህ፡ማየት፤ፍላጎታችን፡ደግሞ፡አንተን፡የሥልጣን፡ባለቤት፡ማድረግ፡ነዉ።አላማችን፡ትልቅ፡ግባችን፡ሠፊ፤መንገዳችን፡ዉስብስብ፡ነዉ።አንዳንዴ፡መዝለል፡ሲያስፈልግን፡ወደሁዋላ፡መንደርደር፡የግድ፡ነዉና፡ይህ፡የጀመርነዉ፡ጉዞ፡አዝጋሚ፡ሊሆን፡ይችላል።ትልቁ፡ቁምነገር፡ወደ፡ግባችን፡ለመድረስ፡ላፍታም፡ቢሆን፡መቆም፡እንደሌለብን፡ማወቁ፡ ነዉ።